# <u>በፓሪስ እና አከባቢው የሚገኙ የዳያስፖራ አባላት ለአምስት ዓመቱ ዕቅድ እና ለታላቁ የህዳሴ ግድብ መገንባት ያላቸውን ድጋፍ ገለጹ ፡፡</u>

አገራችንን በወሳኝ ሁኔታ ሊለውጥ የሚችል የ 5 ዓመት የእድገትና ለውጥ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች ከሚገኙ የዳያስፖራ አባላት ጋር በየአህጉሩ ውይይት እየተደረገ እንደሆነ ይታወቃል ፡፡

የዚሁ ውይይት አካል የሆነው ፕሮግራም በፓሪስና አከባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያንም በአንዳንድ ጸረ ልማት ግለሰቦች «በስብሰባው አትሳተፉ» ፕሮፖጋንዳ ችላ ብለው እ.ኤ.አ ኤፕሪል 16 ቀን 2011 በተዘጋጀው ስብሰባ ላይ በመገኘት በአገራችን እየተካሄዱ ስለሚገኙ የልማት ስራዎች ላይ ውይይት አድርገዋል፡፡

አምባሳደር ተሾመ ቶጋ ባለፉት ዓመታት ስለተመዘገቡ የልማት ግቦች፤እነዚህን የልማት ግቦች መሰረት በማድረግ የአገራችንን ድህነት በግማሽ ለመቀነስ ዓላማ ያደረገ የአምስት ዓመት የእድገትና ለውጥ ዕቅድ በመንግስት ተዘጋጅቶ ወደ ትግበራ መገባቱን፤የትግበራው አንዱ አካል የሆነው ታላቁ የህዳሴ ግድብ ለመገንባትም የመሰረት ድንጋይ መቀመጡን ጨምሮ የእቅዱ ዋና ዋና ጭብጦች እና ዳያስፖራው ለእቅዱ ተግባራዊነት በምን መልኩ ሊሳተፍ እንደሚችል ገለጻ አድርገዋል ፡፡

ከገለጻው በኃላ ተሳታፊዎቹ፤

- ለዘመናት የሌሎች አገሮች ሲሳይ የነበረው የአባይ ወንዛችን ላይ የልማት ስራ ለመስራት በመንግስት እቅድ መያዙና ይህ ተግባር ደግሞ በእኛ ዘመን እየተተገበረ በመሆኑ ከፍተኛ ኩራት ተሰምቶናል፤
- ስለ አባይ ጉዳይ ማውራት መቻላችን እራሳችንን ቀና አድርገን እንድንሄድ አስችሎናልና ይህን ላደረገ መንግስት እናመሰግናለን፤
- ለዕቅዱ ተፈጻሚነት ከኛ የሚጠበቅብንን ሁሉ ለማበርከት ዝግጁ ነን፤
- ግድቡ ሲሰራ ግብጽን ከመሳሰሉ አገሮች ሊሰነዘርብን የሚችል አደጋ ለመከላከል አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲደረግ፤
- ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ልዩነታችንን ወደ ጎን በመተው አንድ ሆነን እቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ መረባረብ እንደሚገባ ገልጸዋል ፡፡

በመጨረሻም ለግድቡ መሰራት የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ፤በቡድንም ሆነ በግል ቦንድ ለመግዛት እንዲሁም በመንግስት የሚጠየቁትን አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ቃል በመግባት ስብሰባው ተጠናቋል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ኤምባሲው